# ***ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ***

***ባይሳ ዋቅ-ወያ***

****

ሰሞኑን የኢህአዴግ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያስተላለፋቸውን ሁለት ውሳኔዎች በተመለከተ ዜጎች ከያቅጣጫው የተሰማቸውን ገልጸዋል፣ በመግለጽም ላይ ናቸው። ነገሩ ሳይታሰብ በድንገት የተከሰተ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግ መንግሥት ዘመን ሊከሰት ይችላል ብለን ስላልጠበቅን፣ ብዙዎቻችንን ግራ አጋብቷል።

ከውሳኔው **ያስደሰተኝ** ትልቁ ነገር ባድሜና ሌሎች ተጎራባች ግዛቶችን ለኤርትራ ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ለመመለስ "መወሰኑ" ነው። ይህ ከአስራ አምስት ዓመት በፊት መፈጸም የነበረበት ስለሆነ ዛሬ ከብዙ መዘግየት በኋላ ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑ፣ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ሕግ አክባሪ መሆኗን የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ሁሉ ዓመታት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አገራችንን "እንደማይታመን ተደራርዳሪ" አድርጎ በመጥፎ ዓይን ከመታየት ገላግሎናል። በርግጥ እነዚህን ቦታዎች ለኤርትራ ላላመስጠት ሲባል ወደ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮቻችን ስለተሰውበት ዛሬ ያ ሁሉ ደም የፈሰሰበት የአገር ጉዳይ እንዳልነበር ሆኖ እነዚህን መንደሮች ለኤርትራ መልሶ መስጠቱ፣ እንደሰው ልጅ ማንኛችንም ቅር ሊለን ይገባል። ህወሃት ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ባደረገው የአስራ ሰባት ዓመት ትግል ጊዜም የኢትዮጵን የግዛት አንድነትና ልዑላዊነት ማስከበርያ ሲባል የፈሰሰው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች (ወያኔ የደርግ ወታደሮች የሚላቸው) ደምም ከዚሁ ጋር በተጓዳኝነት የሚታይና ለዘላለም መረሳት ያለበት ጉዳይ ነው። ሁለቱ ዕብሪተኛ መሪዎች ያለሁለቱ ሕዝቦች ፈቃድ በሕዝቦቻችን ላይ ባወጁት አላስፈላጊ ጦርነት መዘዝ የብዙ መቶ ሺህ ዜጎቻችን ሕይወት ማለፉ ብቻ ሳይሆን፣ ሳይፈረድልን ተፈርዶልናል በሚል ዓይን ያወጣ ውሸትና ዕውን ሊሆን በማይችል ተስፋ ህዝባችንን አሞኝቶ ለዚህ ሁሉ ዓመት ወንድማማችና እህትማማች ሕዝቦችን አጣልቶ ማኖሩ አላስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት፣ ለተሻለ የጉርብትና ኑሮና ብሩኅ ነገ ሲባል ይህንን የዘገየን ውሳኔ በተግባር ለመተርጎም የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህንን ውሳኔ ማሳለፉ ግን ትልቅ ማስተዛዘኛ ሊሆነን ይገባል ባይ ነኝ። ከዚህ በኋላ በሁለቱ አገሮችና ሕዝቦች መካከል ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት በትክክል መተንበይ ባይቻልም፣ ዶ/ር ዓቢይም እንዳሉት ይህ "የሞት-አልባ ጦርነት" ሁኔታ ማክተሙ በራሱ ትልቅ እፎይታ ነው። ዛሬ በነዚህ ቦታዎች ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች የወደፊት ዕጣ ፋንታ ግን ከኤርትራ መንግሥት ጋር <u>መኖር ያለበት ውይይት </u>እንደተጠበቀ ሆኖ!

የውሳኔው ሁለተኛው ክፍል ያዘለው፣ በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበሩትን ተቋማት (ቴሌ፣ አየር መንገድ፣ መብራት ኃይልና ምድር ባቡር ወዘተ) <u>መንግሥት አብዛኛውን ሼር ይዞ</u> ቀሪውን ለባለ ሃብቶች መሸጥ የሚለው ውሳኔ ብዙዎቻችን ያልጠበቅነው ጉዳይ በመሆኑ የተለያየ ስሜት ነው የተሰማን። በውሳኔው መሰረት ***መንግሥት አብዛኛውን ሼር እንዲይዝ*** ተደርጎ መወሰኑ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ በብዙ የአውሮፓ ሃገራት በተግባር የዋለና ህዝብን ከስግብግቡና ጨካኙ ካፒታሊዝም ለመታደግ የታቀደ በመሆኑ ከልብ የሚደገፍ ውሳኔ ነው። ካፒታል በተፈጥሮው ትርፍን እንጂ የሕዝብን ጥቅም ስለማያስቀድም የመንግሥት በነዚህ ተቋማት ውስጥ አብላጫ ሼር መያዝ የግብር ከፋዩን ዜጋ መብት ለማስከበር ይረዳዋልና! ግን ደግሞ፣ ትናንት "የምትታለብ ላም አንሸጥም" የተባለለት ቴሌና፣ ምንም እንኳ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ በአትራፊነቱ ለናሙና የሚጠቀሰውን የኢትዮጵያ አየር ኃይልን <u>ለባለሃብቶች ለመሸጥ</u> መወሰኑ ግራ ቢያጋባንም፣ እንደ አንድ ግለሰብ ዜጋ ግን፣ መንግሥት እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው አገሪቷ ያጋጠማት አንዳች ዓይነት ችግር ቢኖር ነው እንጂ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሕዝብን ጎድቶ ለባለኃብቶች የሚያደላበት ምክንያት አልታይ ብሎን ብዙ ዋዠቅን። መጨረሻ ላይ እሳቸውም ትናንት ለፓርላማ ቀርበው እቅጩን ከተናገሩት እንደተረዳነው ችግሩ ያገሪቷ በዕዳ መዘፈቅ እና ተያይዞም ዕዳውን ለመክፈል የሚያስችል ***የውጭ ምንዛሪ እጥረትን*** ለመወጣት መሆኑን ነው። ይህ እንግዲህ ለምን ሊሆን ቻለ? የተበደርነው ገንዘብ ምን ዓይነት ፕሮጀክት ላይ ውሎ ነው የከሰርነው? በግለሰቦች ተዘርፎ ካገር ውጪ ተግዞ ከሆነስ ሌቦቹ የሰረቁትን መልሰው እንዲያመጡ ምንስ ዓይነት እርምጃ ተወስዷል? አሁን ለባላኃብቶች እንዲሸጡ የተወሰኑ ተቋማቱስ የጎደላቸው ምርታማነት ነው ወይስ አስተዳደር? ችግሩ አስተዳደራዊ ከሆነስ ያ ክፍተት እስካልተሟላ ድረስ ለባለኃብቶች መሸጣቸው ዕውን መፍትሄ ያመጣልን? ሌሎች ብዙ ብዙ ጥቄዎችን ማቅረብ ይቻላል። የዶ/ር ዓቢይ የፓርላማው ንግግር እነዚህን ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል መልሶልኛል።

የውሳኔው ወቅታዊነት በተለያየ መንገድ ተተችቷል። አንዳንዶች የሚሉት፣ "የተደራጁ ሌቦች" አሁንም የባለሥልጣናቱ ሙሉ ድጋፍ ስላላቸው ሆን ብለው እነዚህን ተቋማት ለባለሃብቶች እንዲሸጡ አስወስነው ሊገዟቸው አቅደው ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ፣ እንዲሸጥ መወሰኑ፣ መንግሥት የአብዛኛው ሼሩ ባላቤት እስከሆነ ድረስ ተቋማቱን ፕራቬታይዝ ማድረግ በራሱ ምንም አደጋ አይኖረውም ባይ ናቸው። በበኩሌ የዶ/ር ዓቢይ በንግግራቸው ውስጥ ደጋግመው ስለነዚህ "የተደራጁ ሌቦች" በምሬት በያደባባዩ ማንሳት፣ በሌቦቹ ላይ አንዳች እርምጃ ለመውሰድ የተዘጋጁ ናቸው ብዬ ስለማምን፣ በውሳኔው ውስጥ የሌቦቹ እጅ አለበት የሚለውን ለመቀበል ያስቸግራኛል። እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችንን ያሳሰበን ጉዳይ ግን፣ ከሌቦቹ ውጪ እነዚህን ተቋማት በውጭ ምንዛሪ ሊገዙ በሚችሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ማንነት ላይ ነው። ትንሽ ላብራራ።

---

[1] ጸሃፊው ቀደም ሲል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባላሥልጣን የነበሩ የዓለም አቀፍ ሕግ ባለሙያ ናቸው።

የውጭ ምንዛሪ በርግጥ ለህዛባችን የአየርና የውኃ ያህል አስፈላጊ በመሆኑ እርምጃው የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የግዴታ ነውና ውሳኔው አግባብ አለው ባይ ነኝ። ተያያዥ የሆኑ ሁለት ዕውኔታዎችን ማንሳቱ ግን ተገቢ ይመስለኛል።

***አንደኛው፣*** በእነዚህ አሁን ለገበያ ከቀረቡት ተቋማት ውስጥ መንግሥት አብዛኛውን ሼር ይዞ አናሳውን ክፍል ነው ለሽያጭ የሚያቀርበው፣ (ቢያንስ ቢያንስ 51% በጁ ያስቀራል ማለት ነው)። ስለዚህ የምናወራው ስለ 49% ሼር ጉዳይ ነው ማለት ነው። ***ሁለተኛው፣*** የሽያጩ ዋና ዓላማ የውጭ ምንዛሪ ፍለጋ እስከሆነ ድረስ፣ ገዢዎቹ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ባላኃብቶች ናቸው ማለት ነው። በሕጉ መሰረት ከሄድን፣ "የተደራጁ ሌቦቻችን" በጓሮ ገብተው እንደገና በነዚህ ተቋማት ሼር ገዝተው ዘረፋቸውን ሊቀጥሉበት ይችላሉ የሚባለው ፍራቻ ዕውን ሊሆን አይችልም ማለት ነው። ምክንያቱም፣ *በመጀመርያ ደረጃ* ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ በሕጉ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ምንዛሪ አካውንት ሊኖራቸው አይችልም፣ *በሁለተኛ ደረጃ፣* በውጭ ምንዛሪ ያላቸውን ሃብት ደግሞ አሸሽተው ውጭ አገር ነውና ያካበቱት ነዋሪነታቸው ኢትዮጵያ ሆኖ እያለ፣ "የቆሸሸውን" ገንዘብ "አጽድተውት" በስውር በነዚህ ተቋማት ውስጥ ሼር ለመግዛት ቢሞክሩ ድርጊቱ ተጨማሪ ወንጀል ይሆናል ማለት ነው። ባጭሩ፣ ሼሮቹ የሚሸጡት በውጭ ምንዛሪ ብቻ ስለሆነና አገር ቤት ያሉት "የተደራጁ ሌቦች" ወገኖቻችን ደግሞ ባገር ቤት ውስጥ ሕጋዊ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ስለሌላቸው፣ ከገበያው ውጭ ናቸው ብለን ወደሚቀጥለው እንለፍ።

የተፈለገውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እንግዲህ መንግሥት ያለው ብቸኛ ምርጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ በሆነ መንገድ የውጪ ምንዛሪ ያላቸውንና እነዚህን ተቋማት ለመግዛት  የሚችሉ ግለሰቦችን ወይም ደግሞ ከኢትዮጵያ ወጣ ብሎ ባለኃብቶችን ማደን ነው። ዓለማችን ከተስፋፊ መንግሥታት ጀምሮ እስከ ግለሰብ ቱጃሮች ድረስ ደካማ አገሮችን እየፈለጉ "በአራጣ ለማበደር" ወይም "በችግር ጊዜ ቀድሞ ደራሽ" ሰፍሳፎችና ስግብግቦች የተሞላች ስለሆነ፣ የገዢ ችግር የሚያጋጥመን አይመስለኝም። በተለይም ደግሞ አሁን ለሽያጭ የቀረቡት  ሸቀጦቹ በጣም አጓጊና አትራፊ ስለሆኑ! በኔ ግምት ለመንግሥት ልዩ የቤት ሥራ ይሆነዋል ብዬ የምገምተውና መሆንም ያለበት፣ ለየትኛው ገዢ ቅድሚያ እንደሚሰጥ ነው። ትንሽ ላብራራ!

ከልምድ እንደምናውቀው የሻጭ ዋና ዓላማ ሸቀጡን በቶሎ ሽጦ ገንዘቡን ኪሱ ከትቶ ወደ ቤቱ መመለስ ነው። ሸቀጥ ለፀሃይ ተጋልጦ ሲንቃቃ ከዋለ ፈላጊው ብዙ አይደለም ማለት ነውና ዋጋው ይቀንሳል። ተፈላጊ ሸቀጥ ደግሞ ፈረንጆች እንደሚሉት "ትኩስ ኬክ" ነው። ፈላጊው ብዙ ነው። በኔ ግምት እነዚህን ሰሞኑን መንግሥት ፕራይቬታይዝ ለማድረግ ለገበያ ያቀረባቸው ሸቀጦች "ትኩስ ኬኮች" ናቸው። ከቻይና ወይም የስዊስ ባለኃብቶች እንዲሁም የሕንድና የዓረብ ቱጃሮችን ጨምሮ ብዙ የውጭ አገር ባላሃብቶች እንደሚቀራመቷቸው እርግጠኛ ነኝ። ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ግን፣ ከአቶ አላሙዲን ውጪ ከነዚህ ግዙፉን ባላሃብቶች ጋር ሊወዳደሩ የሚችሉ ያሉ አይመስለኝም። እነዚህን ሰሞኑን ለሽያጭ ለገበያ የቀረቡት ተቋማትን በተመለከት ግን፣ ሀ) መንግሥት ሸቀጦቹን ላንድ ቀድሞ ለመጣ ባለኃብት በቶሎ ሽጦ ከመገላገል፣ እየቀነጣጠበ ለብዙ ባላኃብቶች ቢሸጣቸውና፣ **ለ**) በቅንጣቢ እንዲገዙ ከሚፈቀድላቸው ባላኃብቶች መካከል ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ያላቸውና በሕጋዊ መንገድ የውጪ ምንዛሪ ሊኖራቸው የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ወይም ደግሞ በውጭ አገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ባይ ነኝ። የጽሁፌም ዓላማ ይህንኑ ለማሳመን ነው። ለሽያጭ የቀረቡት የግል ንብረት ሳይሆኑ የሕዝብ ሀብት ናቸውና፣ መንግሥት የንግድ ተቋማቱን የመሸጥ ብቻ ሳይሆን ለማን መሸጥ እንዳለበትም ለመወሰን ያገሪቷንና የወከለውን ሕዝብ ጥቅም ትልቅ ግንዛቤ ውስጥ የመክተት ግዴታ አለበት ባይ ነኝ።

በተለያዩ አገራት ተበታትነው የሚኖሩ ከሚሊዮን በላይ የሆኑ **ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣** መንግሥት ሁኔታውን ካመቻቸላቸው ያገሪቷን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ከሞላ ጎደል ሊያሟሉ ይችላሉ የሚል ሙሉ እምነት አለኝ። ችግሩ ግን አሁን በሥራ ላይ ያለው ያገሪቷ ሕግ፣ መሰረታዊውን የኤኮኖሚ ሕግን መሰረት ያደረገ ሳይሆን፣ ፊውዳላዊ በሆነ የምቀኝነት ባህል ላይ የተመሰረተ በመሆኑና ኢሕአዴግ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ተቃዋሚ አድርጎ ይፈርጅ ስለነበረ ባገሪቷ ውስጥ ባሉት የንግድ ተቋማት (ባንክ፣ ኢንሹራንስ ወዘተ) ሼር እንዳይገዙ ይከለክላል። ስለዚህ፣ ዶ/ር ዓቢይ እንደ ቤት ሥራ መውሰድ ያለባቸው የመጀመርያው ጉዳይ ቢኖር ይህንን የመንግሥት ለውጭ ምንዛሬ ያለውን ጥማትንና **የትውልደ ኢትዮጵያዊውን** በየንግድ ተቋማቱ ውስጥ ሼር ለመግዛት ያላቸውን ፍላጎት እንዴት አድርጎ ማጣጣም እንደሚቻል መወሰኑ ይመስለኛል። በዚህ ዙርያ ያለው ትልቁ ችግር፣ ጓደኛዬ ካሳሁን እንዳለው፣ የኢትዮጵያውያን ልዩ እሴት የሆነው "ምቀኝነት" ብቻ ይመስለኛል። እሱን ወደ ጎን አድርገን ዓላማው ላይ ብቻ ካተኮርን፣ ያገሩን ማሳ ባገሩ በሬ የማናርስበት ምክንያት የለም ባይ ነኝ። የኢትዮጵያ ባንዲራ የሚያውለበልበውን የኢትዮጵያ አየር መንገዳችንን ሼር ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን በውጪ ምንዛሪ እንዲገዙ ቢደረግ፣ ብሔራዊ ስሜት ከፍ ይላል፣ መንግሥት ደግሞ አስፈላጊውን የውጪ ምንዛሪ ያገኛል። የሼሩ ገዢዎችም መንግሥትም እኩል አሸናፊ ይሆናሉ ማለት ነው። ምናልባት በውጪ ምንዛሪ ሼሮቹን ሊገዙ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ብዙ ላይሆን ይችላል። ያ ከሆነ ግን መንግሥት እስከተቻለ ድረስ ከነዚህ ወገኖቻችን አሟጥጦ ካበቃ ባኋላ ለውጭ ባላኃብት ለሽያጭ ቢያቀርብ ትክክለኛ አካሄድ ይመስለኛል።

ስለዚህ በኔ ግምት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት **ሁለት** ዓበይት እርምጃዎችን መውሰድ አለበት የሚል ሃሳብ አለኝ። የመጀመርያው ያለምንም ቅድም ሁኔታ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በነዚህና በመሳሰሉት ተቋማት ውስጥ **በውጭ ምንዛሪ ሼር እንዲገዙ የሚፍቀድ ደንብ ማውጣት አለበት**። መንግሥት እያየ እንዳላየ ለመሆን ፈልጎ ነው እንጂ፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እኮ የሕዳሴ ግድብን ሼር (ሴኩሪቲ ቦንድ) በውጭ ምንዛሪ በመግዛት ያገራቸውን ማህበረሰባዊና ኤኮኖሚያዊ ችግር ለመቅረፍ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እያደረጉ ነው። የሕዳሴ ግድብን ሼር እየገዙ በባንክና በኢንሹራንስ ደግሞ ሼር መግዛት አትችሉም ማለት ትርጉም አልባ ይመስለኛል። ስለዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በነዚህ ተቋማት ውስጥ ሼር የመግዛት ዕድሉ ከተሰጣቸው፣ አገሪቷ የምትፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንም ባገራቸው ታላላቅ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ሼር በመግዛታቸው ከመዋዕለ ንዋይ ጥቅሙ በላይ በመብራት ኃይል፣ ቴሌና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ሼር ስላላቸው የኢትዮጵያዊነት ግዴታቸውንም ይወጣሉና ልባዊ ደስታ ይሰማቸዋል። መንግሥትም በዚህ ጉዳይ ላይ ያስተላልፋል ብዬ የማስበው ውሳኔ፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ከትውልድ አገራቸው ጋር የሚያተሳስርና ለወደፊትም ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን ያካበቱትን የሥራ ልምድና ዕውቀት ይዘው ወዳገራቸው እንዲመለሱ እንደሚገፋፋቸው ሙሉ እምነት አለኝ።

ሁለተኛውና መንግሥት በጥብቅ እንዲያስብበት የሚገባው ጉዳይ ደግሞ፣ የግለሰቦችን ሞኖፖሊና ምናልባትም እነዚህ "የተደራጁ ሌቦች" በጓዳ በር ገብተው ውጭ አገር ያካበቱትን ሃብት በሌላ ዘዴ ሼሮቹን በገፍ እንዳይገዙ **የመከላከያ አጥር ማበጀት ነው።** በኔ ግምት፣ መንግሥት በውሳኔ ደረጃ ማስቀመጥ ያለበት አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር፣ አንድ ግለሰብ ሊገዛ የሚችለውን የሼር ብዛትን (ጣራ) በሕግ መገደብ ነው። በዚህ አኳኋን፣ ተቋማቱን ከግለሰብ ሞኖፖሊ ለማዳን ብቻ ሳይሆን ብዙ ግለሰቦች እንደያቅማቸው ሼሮቹን እንዲገዙ ዕድል ይሰጣቸዋል። **በሌላ አነጋገር ተቋማቱ የጥቂት ግለሰብ ባላኃብቶች ሳይሆኑ የብዙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሃብት ይሆናሉ ማለት ነው።** ዓጼ ኃይለ ሥላሴ፣ የልጃቸው የልዑል መኮንን ሞት ምክንያት በማድረግ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፍስ ውከፍ አንዳንድ ብር አዋጥቶ በልጃቸው ስም የሚጠራ አንድ ሆስፒታል እንዲሠራ "በፈቀዱት" መሠረት ነበር የያኔው የልዑል መኮንን የዛሬው የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተሰራው። መሪሁ ሃምሳ ሎሚ ላንድ ሰው ሸክም፣ ላምሳ ሰው ግን ሽቱ ነው የሚለው ነው። በሌላ አነጋገር፣ ጥሩ ጥሩ የሚሸት ቀላል ሸክምን መሸከም ማለት ነው። ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሆነው ትውልደ ኢትዮጵያዊ፣ ለራሱና ለቤተሰቡ ብቻ፣ (ኢትዮጵያው ውስጥ ያሉትንም ወላጆቹንና ቤተዘመዱን ጨምሮ) ሼሩን ቢገዛ ቢያንስ ቢያንስ፣ እነዚህ ተቋማት የአስር ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ይሆናሉ ማለት ነው።

ከባዕዳን ባለሀብቶች ይልቅ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሼሮቹን ቢገዙ አገሪቷ ብዙ ትጠቀማለች የምልበት አሳማኝ ምክንያቶች አሉኝ።

**አንደኛ፣** የሼሮቹ ባላቤቶች ባዕዳን ግለሰቦች ሳይሆኑ በውጪ ምንዛሪ ሼሮቹን ሊገዙ የሚችሉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስለሚሆኑ ያገራችን ክብር መገለጫ የሆኑትን ለምሳሌ የአየር መንገዳችንን የመብራት ኃይሉንና ቴሌን ገዝተው **ሕዝባዊ ሀብታችንን በሕዝቡ ልጆች** እጅ እንዲቀር ያደርጋሉ ማለት ነው።

**ሁለተኛ፣** ሼሮቹ በጥቂት ግለሰቦች ሳይሆን በብዙ ሺዎች ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እጅ መግባቱ፣ **ሞኖፖሊን ያቀጭጫል።** ምንም እንኳ መንግሥት ያብዛኛው ሼር ባለቤት ቢሆንም፣ ሌላ የሚገዳደረው ማለትም 49%ቱን ባለቤት የሆነው አንድ ጠንካራ ባለሀብት አይኖርም ማለት ነው።

**ሶስተኛ፣** በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያኖቹ ከሼሮቹ የሚያገኟቸውን ትርፍ (ዲቪዴንድ) **ካገር አያሸሹም።** ገንዘቡ ባገሪቷ ውስጥ መቅረቱ ደግሞ ያጋሪቷን ኤኮኖሚ በተጨማሪ ይደጉማል፣ በላሼሮቹ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ባገኙት ትርፍ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት ሁኔታ!

በዚህ አርዕስት ዙርያ ከኔ በተሻለ መልኩ ሙያውና ልምዱ ያላችሁ ዜጎች፣ በበለጠ ብታብራሩልን ደስ ይለናል።

በቸር ይግጠመን።

****

ጄኔቫ፣ ሰኔ 20 ቀን 2018 ዓ/ም
wakwoya2016@gmail.com